## *ቀኖና ክፍል 2*

### *ቀኖና፥ ምን ማለት ነወ?*

### ሥርዓት ማለት ነው።

### *ቀኖና መቼ እና ማን፥ በየትስ ተጀመረ?*

### በ51 ዓ/ም ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ጀመሩት።

### *ጥንቱን ሕግ ለኃጥአን እንጅ፥ ለጻድቃን አልተሠራም ነበር።*

ወደ መቄዶንያ በሔድኩ ጊዜ አንዳንዶች ልዩ ትምህርትን እንዳያስተምሩና፥ ወደ ተረት፥ መጨረሻም ወደ ሌለው ወደ ትውልዶች ታሪክ፥እንዳያደምጡ ልታዝዛቸው በኤፌሶን ትቀመጥ ዘንድ ለመንኩህ። እንደዚህ ያሉ ነገሮች ክርክርን ያመጣሉና። በእምነት ግን ላለ፥ለእግዚአብሔር መጋቢነት አይጠቅሙም። የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹህ ልብና ከበጎ ሕሊና፥ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው። ከእነዚህም አንዳንዶች ስተው የሚሉትን ወይም ስለእነርሱ አስረግጠው የሚናገሩትን ሳያስተውሉ፥ የሕግ አስተማሪዎች ሊሆኑ እየወደዱ ወደ ከንቱ ንግግር ፈቀቅ ብለዋል።

ነገር ግን ሰው እንደሚገባ ቢሠራበት ሕግ መልካም እንደሆነ እናውቃለን። ይኸውም ለበደለኞችና ለማይታዘዙ፥ለዐመፀኞችና ለኃጢአተኞች፥ቅድስና ለሌላቸውና ለርኩሳን፥ አባትንና እናትን ለሚገድሉ፥ ለነፍስ ገዳዮችና ለሴሰኞች፥ከወንድ ጋርም ለሚተኙ፥ በሰዎችም ለሚነግዱ፥ለውሸተኞችም፥ በውሸትም ለሚምሉ፥የቡሩክ እግዚአብሔርንም ክብር እንደሚገልጥ ለእኔ አደራ እንደተሰጠኝ ወንጌል የሆነውን ደኅና ትምህርት ለሚቃወም፥ለሌላ ነገር ሁሉ፥ ሕግ እንደተሠራ እንጅ፥ለጻድቅ እንዳልተሠራ ሲያውቅ ነው።»....<u>፩ ጢሞ 1፥4-11</u>

«ፈሪሳውያንና ከጻፎች ወገን፥ከኢየሩሳሌም የመጡትም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንድ በርኩስ ማለት ባልታጠበ እጅ እንጀራ ሲበሉ አዩ። ፈሪሳውያንና አይሁድም ሁሉ፥የሽማግሎችን ወግ ሲጠብቁ፥ እጃቸውን ደኅና አድርገው ሳይታጠቡ አይበሉምና፥ ከገበያም ተመልሰው ካልታጠቡ አይበሉም፣ ጽዋንም ማድጋንም የናስ እቃንም አልጋንም እንደማጠብ ሌላ ነገር ሊጠብቁት የተቀበሉት ብዙ አለ። ፈሪሳውያንም ጻፎችም ደቀ መዛሙርትህ እንደሽማግሎች ወግ ስለምን አይሄዱም? ነገር ግን እጃቸውን ሳይታጠቡ እንጀራ ይበላሉ ብለው ጠየቁት። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፥-ኢሳይያስ ስለእናንተ ስለግብዞች፥-ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፥ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል፣ተብሎ እንደተጻፈ በእውነት ትንቢት ተናገረ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ ጽዋን ማድጋንም እንደማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ፣ይህንም የመሰለ ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ።

እንዲህም አላቸው፥-ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል። ሙሴ፥- አባትህንና እናትህን አክብር፥ ደግሞ፥- አባቱን ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ብሎአልና። እናንተ ግን ትላላችሁ፥- ሰው አባቱን ወይም እናቱን፥- ከእኔ የምትጠቀምበት ነገር ሁሉ ቁርባን ማለት መባ ነው ቢል፥ ለአባቱና ለእናቱ ምንም እንኳ ሊያደርግ ወደ ፊት አትፈቅዱለትም። ባስተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ።

እንደዚሁም ይህን የሚመስል ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ።
ደግሞም ሕዝቡን ጠርቶ፥- ሁላችሁ እኔን ስሙ አስተውሉም።
ከሰው የሚወጡት ሰውን የሚያረክሱ ናቸው እንጅ፤ከሰው ውጭ የሚገባውስ ሊያረክሰው የሚችል ምንም የለም። የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ አላቸው። ከሕዘቡ ዘንድ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ምሳሌውን ጠየቁት። እርሱም እናንተ ደግሞ እንደዚህ የማታስተውሉ ናችሁን? ከውጭ ወደ ሰው የሚገባ ሊያረክሰው ምንም እንዳይችል አትመለከቱምን? ወደ ሆድ ገብቶ ወደ እዳሪ ይወጣል እንጅ ወደ ልብ አይገባምና፣ መብልን ሁሉ እያጠራ አላቸው።እርሱም አለ፥- ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ያ ነው። ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጎምጀት፤ክፋት፥ተንኮል፥መዳራት፥ምቀኝነት፥ስድብ፥ትእቢት፥ ስንፍና ናቸውና፣ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል።»............ማር 7፥1-23
ከዚህ ላይ ጌታ ያስተማረው ትምህርት፥የመሰለው ምሳሌ፥ሐዋርያትን ከፈሪሳውያን ወግ ሲጠብቃቸው እናያለን።ጌታ ያን ጊዜ ይህን መልስ ባይሰጥ ኑሮ፥ ሐዋርያት የፈሪሳውያንን ትብትብ ለመሸከም በተገደዱ ነበር።

## ቀኖና ለምን አስፈለገ?

፩. ቤተ ክርስቲያንን ከቢጽ ሐሳውያንና ከመናፍቃን ትምህርት ለመጠበቅ፣
፪. ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓት ለመምራት፣
፫. ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመናፍቃን መጻሕፍት ለመለየት።

፩. ቤተ ክርስቲያንን ከቢጽ ሐሳውያንና ከመናፍቃን ትምህርት ለመጠበቅ።
«አንዳንዶችም ከይሁዳ ወረዱና፥-እንደሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም ብለው ወንድሞችን ያስተምሩ ነበር። በእነርሱና በጳውሎስ በበርናባስም መካከል ብዙ ጥልና ክርክር በሆነ ጊዜ ስለዚህ ክርክር ጳውሎስና በርናባስ ከእነርሱም አንዳንዶች ሌሎች ሰዎች ወደ ሐዋርያት ወደ ቀሳውስትም ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ዘንድ ተቆረጠ።»......................................................................................................የሐዋ 15፥1
«ከፈሪሳውያን ወገን ግን ያመኑት አንዳንዶቹ ተነስተው፥-ትገርዙአቸው ዘንድ እና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ታዝዙአቸው ዘንድ ይገባል አሉ።»...................የሐዋ 15፥5
ሐዋርያትና ቀሳውስትም ስለዚህ ነገር ለመመካከር ተሰበሰቡ።
ከብዙ ክርክርም በኋላ ጴጥሮስ ተነስቶ እንዲህ አላቸው።.....እንግዲህ አባቶቻችንና እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን እግዚአብሔርን አሁን ስለምን ትፈታተናላችሁ? ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደእነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን።»..........................................................................የሐዋ 15፥10

## ሐዋርያት በሲኖዶስ የወሰኑት ሙሉ ቃል፤

«ሐዋርያትና ቀሳውስት ወንድሞችም፥በአንጾኪያና በሶርያ፥በኪልቅያም ለሚኖሩ ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ ወንድሞች ሰላምታ ያቀርባሉ። ያላዘዝናቸው ሰዎች ከእኛ ወጥተው፥-ትገረዙ ዘንድና ሕግን ትጠብቁ ዘንድ ይገባችኋል ብለው ልባችሁን እያወኩ በቃል እንዳናወጡአችሁ ስለሰማን፥ስለጌታችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነፍሳቸውን ከሰጡት ከምንወዳቸው ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር የተመረጡትን ሰዎች ወደ እናንተ እንልክ ዘንድ በአንድ ልብ ሁነን ፈቀድን። ራሳቸውም ደግሞ በቃላቸው ያንኑ ይነግሩአችሁ ዘንድ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል።

ሠ. «በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ፥ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፣ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።».......................................፪ ጴጥ 1፥20

እግዚአብሔር የፈቀደላቸው ቅዱሳን ነቢያትና ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ንጹሑን የስንዴ ዘር ቅዱሳት መጻሕፍትን ጽፈው ለቤተ ክርስቲያን ካስረከቡ በኋላ ጠላት በስንዴው መካከልእንክርዳድ እንደዘራ ሁሉ፥ ቢጽ ሐሳውያንና የፍልስፍና ሰዎች ልዩ ልዩ የሐሰት መጻሕፍትን በሐዋርያት ስም እየጻፉ፥ቤተ ክርስቲያንን ለማደናገር ሞክረው ነበር። በመሆኑም በመንፈስ ቅዱስ የተጻፉትን ለይቶ ለማወቅና የቢጽ ሐሳውያንን የሐሰት መጻሕፍት ውድቅ ለማድረግ ቀኖና መጻሕፍት አስፈለገ።

- ***<u>የቀኖና መጻሕፍት ምንጮች፤</u>***
- 1. 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት፣ ቀኖና 85፣
- 2. ሲኖዶስ ዘቤተ ክርስቲያን፣ ትእዛዝ 57/56፥ ቀኖና 56፣
- 3. ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጥሊሳት 82፥ቀኖና 81፣
- 4. ሥርዓተ ሐዋርያት ትእዛዝ 80፥ ቀኖና 80፣
- 5. ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጥሊስ 81፥ቀኖና 80፣
- 6. ቀኖና ዘሎዶቅያ፣(ላኦዶቅያ) 60ኛ ቀኖና፣
- 7. ቀኖና ዘቅርጣግና ቀኖና 24/32፣
- 8. መልእክተ አትናቴዎስ መልእክት 39ኛ፣
- 9. ቀኖና ጎርጎርዮስ ቀኖና 1፣
- 10. ቀኖና አምፊሎክዮስ ዘኢቆንዮን ቀኖና 1፣
- 11. ፍትሐ ነገሥት ጉልቄ መጻሕፍት ፀንቀጽ 2፣
- ***<u>ቀኖና ይሻሻላል፣</u>***

ቀኖና የሚሻሻለው ግን በቅዱስ ሲኖዶስ ብቻ ነው።
ማስረጃውንም ከዚህ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

ሀ. «በሥራ ፍጹም የሆነ ሁሉ፥ ጎደሎውን ሊሽረው ይገባልና፣ ስለዚህም የጌታችን ሕግ (ወንጌል) ከእርስዋ የሚቀድመውን (ኦሪትን) ሻረችው እርስዋ ግን (ወንጌል) ልትሻር አይገባትም። ከእርስዋ የሚበልጥ የለምና። እርስዋ የፍጹምነትና የመጨረሻ ፍጽምት ሕግ ናትና።» ........................................................................ፍ/ነገ/ መቅድም ገጽ 7.

ለ. «ምንአልባት እኛ ያጎደልነው ቢኖር በሁላችንም መንፈስ ቅዱስ አድሮብናልና፥እናንተ እንደሚገባ አድርጋችሁ ፍረዱ።» ትእዛ 71፣

ሐ. ከእኛ የቀረ ምንም ቢኖር ኤጲስቆጶስ ይፈጽም። ትእዛዝ 35

መ. የተወደዳችሁ ወንድሞቻችን ሆይ! ቤተ ክርስቲያን በሚገባ ወደ ጸጥታ ወደብ ትመራ ዘንድ ከእኛ የቀረ ምንም ምን ሥርዓት ቢኖር እግዚአብሔር ለሚገባው ሰው ይግለጥለት። ትእዛዝ 47፥

ሠ. እነሆ! በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ለሊቃውንት የሚገባው ነገር ተጽፎአል፣ በእርሱ ላይ እንዲጨምሩ፣ ከእርሱም እንዲቀንሱ በዚህ ውስጥ ያላተፈቀደላቸው ነገር የለም።

ፍ/ነገ/ መቅድም 11

ለጣዖት ከተሠዋ፥ ከደምም፥ ከታንቀም፥ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው
በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና።
ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ፣ጤና ይስጣችሁ።»......የሐዋ 15፥23-29

***፪. ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓት ለመምራት፣***

ሀ. «በከተማዎችም ሲዞሩ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትና ቀሳውስት
የቆረጡትን ሥርዓት ይጠብቁ ዘንድ ሰጡአቸው። አብያተ ክርስቲያናትም በሃይማኖት
ይበረቱ ነበር፣ በቁጥርም ዕለት ዕለት ይበዙ ነበር።»..........................................የሐዋ 16፥4-5

ለ. «ወንድሞች ሆይ በሁሉ ስለምታስቡኝና አሳልፌ እንደሰጠኋችሁ
ወግን ፈጽማችሁ ስለያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ።»..........................................፩ኛ ቆሮ 11፥2

ሐ.« ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ ይህን እላለሁ፣
በሥጋ ምንም እንኳ ብርቅ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና ሥርዓታችሁንም በክርስቶስም
ያለውን የእምነታችሁን ጽንአት እያየሁ ደስ ይለኛል»።..........................................ቆላ 2፥5

መ. «እንግዲያስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ፣ በቃላችንም ቢሆን
ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ።»..........................................፪ ተሰ 2፥15

ሠ. «ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለሥርዓት
ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን።
እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና፥ በእናንተ ዘንድ
ያለ ሥርዓት አልሄድንምና።»..........................................፪ኛ ተሰ 3፥6

ረ. «ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፥ ትንቢት ለመናገር በብርቱ ፈልጉ፣
በልሳኖች ከመናገርም አትከልክሉ፣ነገር ግን ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን።»........፩ኛ ቆሮ 14፥39

ሰ. «ንቁ፥በሃይማኖት ቁሙ፥ ጎልምሱ ጠንከሩ።
በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን»።..........................................፩ኛ ቆሮ 16፥13

***፫. ቅዱሳት መጻሀፍትን ከመናፍቃን መጻሀፍት ለይቶ ለማወቅ።***

ሀ. «የከበርክ ቴዎፍሎስ ሆይ! ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና፥
የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በእኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር፥
ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለተማርከው ቃል
እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትየ በእየተራው
ልጽፍልህ መልካም ሁኖ ታየኝ።»..........................................ሉቃ 1፥1-4

ለ. «በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ፥ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ
ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ። እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም።
የሚያናውጧችሁ፥የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ፥አንዳንዶች አሉ እንጅ።
ነገር ግን እኛ ብንሆን፥ወይም ከሰማይ መልአክ፥ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን
ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን።»..........................................ገላ 1፥6-9

ሐ.«በመጽናትና መጻህፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ
አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።»..........................................ሮሜ 15፥4

መ. «አንተ ግን በተማርከበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን
እንደተማርከው ታውቃለህና፣ከህጻንነት ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን
ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻህፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ
ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና
ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።»...............፪ ጢሞ 3፥14-17

## የዶግማና የቀኖና ማጠቃለያ ሐሳብ፣

### 1.የዶግማ ሐሳብ፣

ሀ. «መዳን በሌላ በማንም የለም፣እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።»......................................................................................የሐዋ 4፥14

ለ. «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፣ አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ».የሐዋ 16፥31

በዚህ ቅዱስ ቃል መሠረት የእግዚአብሔር አንድነቱ ሦስትነቱ የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነቱ፥ ዶግማ ይባላል። ዶግማ የማይጨመርበት፥የማይቀነስበት ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ነው። ማጽደቅና መኮነን የሚችል፥የማይለወጥና የማይሻሻልም ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር የለም፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስም አይባልም፣ ኢየሱስ ክርስቶስም አያድንም የሚል ክፉ ለማስካድ የሚያስገድድ ኃይል ቢነሣ፥የእውነተኛ ክርስቲያን ውሳኔና ምርጫ ሞት ብቻ ነው። «እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን፣ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።» እንዲል............ራእይ 2፥10 ስለዚህ ጽድቅና ኩነኔ፥ሕይወትና ሞት፥ በዶግማ ነውና፥በእምነታችን እስከ ሞት ድረስ ለመጽናት በመንፈስ የጸናን የበረታን፥ በጸሎት የተጋን በእግዚአብሔር ቃልም የታነጽን መሆን አለብን።

### 2. የቀኖና ሐሳብ፣

- ❖ ስለጾም ቀናት ማነስና መብዛት፥ ስለጾም ምግብና ሰዓት፣
- ❖ ስለበዓላት ማነስና መብዛት፥ ስለበዓላት መቸ መሆን እንዲሚገባ፣
- ❖ ስለቅዳሴ ሥርዓት፥በስንት መቸ እንደሚቀደስ፣
- ❖ ስለሴቶችና ወንዶች የመግቢያ በርና መቆሚያ፣
- ❖ ስለሕፃናት በ40 ቀንና በ80 ቀን መጠመቅ፣
- ❖ ስለመስቀል መሳለም፣
- ❖ ስለቅዱስ ሥዕል፣
- ❖ ስለሐዲስ ኪዳን የታቦት አገልግሎት፣
- ❖ ስለቤተ መቅደስ ሥርዓት በሙሉ፣
- ❖ ስለዝክርና ተዝካር፣
- ❖ ስለጸሎተ ፍትሐትና ስለመሳሰሉት ሁሉ የሚደነግግ ነው።

ቀኖና መሠረቱን ሳይለቅ እንደጊዜው ሁኔታ ሊሻሻል የሚችል ሥርዓት ነው።

ስለዚህ፥-

- ❖ ዶግማ አይሻሻልም። ቀኖና ግን ይሻሻል።
- ❖ ዶግማ አይቀነስም። ቀኖና ግን ይቀነሳል።
- ❖ በዶግማ ላይ ምንም አይጨመርም። ቀኖና ግን ይጨመርበታል።
- ❖ ዶግማን እግዚአብሔር ሠራው። ቀኖና ግን በሲኖዶስ የሚሠራ ነው።

ቀኖና ከተሻሻለና ትውልዱ ባደገ ቁጥር አብሮ ካደገ፣ ከተተኪው ትውልድ ጋር አብሮ በአግባቡ ከተዋሐደ፥ቢጨመር እንጅ አይቀነስም። ምክንያቱም ቀኖና ምንም እንኳ በጽድቅና በኩነኔ ውስጥ ባይገባም በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል ያለውን ጽኑ ፍቅር የሚገልጥ ነውና። አንዳንድ ሰዎች፥የሙሴ ሕግ ያድንናል፣ ክርስትናን አንቀበልም፣ በማለት የተሳሳቱ ፈሪሳውያንን ለመገሰጽ፥ወግና ሥርዓት ብቻ እንደማይጠቅም፥ የተናገረውን በመጥቀስ ምእመናንን ያደናግራሉ። ይህ እጅግ በጣም ስህተትም ሀሰትም ነው። የቤተ ክርስቲያናችን መሠረትዋም ጉልላትዋም ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና።